# እምቢኝን እንልመድ

ከመዝገቡ ባየህ

ድሮ በዚያን ጊዜ፣ ትግል መቼ ጠፍቶ፣
አንዴ ከስርዓቱ፣ ሌላም ከተፈጥሮ፣
ሚሊዮን ሰማዕታት፣ ሕይወት ገብረዋል፣
ትግሉ ነው ሕይወቴ፣ እያሉ ወድቀዋል፣
ለብሩህ ቀን ተስፋ፣ መስዋዕት ሆነዋል።
ያኔ የሚሞተው፣ ለሰንደቅ፣ ለእምነት፣
ለለውጥ፣ ለነፃነት፣
ነበረ ለመብት፣ ለሰው ልጅ አርነት፣
ሕዝብ ስልጣን ለማስያዝ፣ በባለቤትነት፣
ዛሬ ዛሬ ደግሞ፣ ቅኝት ተለውጦ፣
ለወጉም ቀረና፣ መሞት ተፈራግጦ፣
እየተለመደ፣ መኖር ለሽልጦ፣
እምቢ ባይ ሲነቀፍ፣ ቡከን ክብር አግኝቶ፣
መንበርከክ፣ መዋረድ ህሊናን አግብቶ፣
ተዳብሎ እየኖረ፣ ልቦናንም አጭቶ፣
ለበርጩማ መሞት፣ ስልጡን አሰኝቶ፣
የትግል ትርጉሙ፣ በዚያው አፈር በልቶ፣
ጀግና ያስብል ጀመር፣ መኖር ጫማ ልሶ፣
ሆድን እየሞሉ፣ ህሊናን አርክሶ።

በእምቢኝ አሻፈረኝ፣ መሞትን አሙተን፣
ክብራችንን እኛ፣ ከብረን ካላስከበርን፣
ጠላት ወዳጅ ላይሆን፣
ሲገለን ሲመትረን፣
መኅንበስ፣ መንበርከክ፣ ነፃነት ላይሰጠን፣
እጅ ሰጥቶ ልመና፣ የትም አያደርሰን!

ትራፊ ለመልቀም፣ በርጩማ ልመና፣
ውጤት አላስገኘም፣ ካቻምናም ሆነ አምና፣
እምቢኝን እንጀምር፣ በእምቢኝ እናምጽ፣
በደም ባጥንታችን፣
ለነፃነታችን፣
የብሩህ ቀን፣
ሐውልት በትግል እናንጽ!

እምቢኝን እንልመድ፣ አይተውም ቀን አይቶ፣
አይከዳም ቀን አይቶ፣
በሕዝብ ትግል ልዋጭ፣ በርጩማ አሸምቶ፣
አያሸበርክም፣ የጠላት ፊት አይቶ!
አያስበረክክም፣ የሰው ጫማ አስልሶ!
ነፃነት ያስገኛል፣ ከድል ጋር አድርሶ።